# ጥርጥር የሌለው አሸናፊነት

**መክብብ ይሁን**

**11-28-14**

ምርጫ 2007 ስድስት ወራት ብቻ ቀረው፣ የሀገር ውስጡም የውጭውም ፅንፈኛ ተቃዋሚ የልዩ ትኩረትና የመወያያ ርዕስ ከሆነ ሰነበተ፡፡ ለታሪክ የሚበጅ የሚተላለፍ አኩሪ ተግባር መፈፀምና አንድም ሳይሰሩ ቁጭ ብሎ እድሜ ዘመንን ከሰማይ በታች የተዘረጋውን ሁሉ በመቃወም በማጣጣል በማቆሸሽ በጥላቻ ተውጦ መንዘፍዘፍ ልዩነቱ እንደ ሰማይና ምድር የሰፋ ነው፡፡ ባደጉት አገሮች አተያይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መኖር የሚደገፍና የሚበረታታ ሲሆን አማራጭ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ሀገራዊና የውጪ ፖሊስንም በአማራጭ መልኩ ለማየት ለመተነተን ያስችላል፡፡

የተቃዋሚ ፓርቲዎች አማራጭና የተሻለ ሀሳብ ይዞ በሕዝቡ ፊት መቅረብ መወያየት በሕዝቡም እንዲዳብሩ መደረጉ ለሀገሪቱ የእኔ ፖሊሲ ወይንም ፖለቲካል ኢኮኖማ በሥራ ላይ ቢውል የበለጠ ልማትና እድገት ብልፅግና ሊያመጣ ይችላል፣ የሀገሪቱም የዜጐችም ሕይወትና የነፍስ ወከፍ ገቢ ይሻሻላል፣ በጤናው፣ በትምህርቱ፣ ማህበራዊ ዘርፉ፣ በኢኮኖሚው ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ያመጣል በሚል ተቃዋሚው ሲከራከር ዳኝነቱንና ፍርዱ የፓርቲዎች ሳይሆን ከምርጫ ሣጥን የሚገኘው የሕዝብ ውሣኔ ነው፡፡

ለሪፐብሊካኑም ፓርቲ ሆነ ዴሞክራቲክ ፓርቲ ሊበራል ፓርቲውም ሆነ የኮንሰርቫቲቭ ፓርቲም ሆነ የቀኝ ወይንም የግራው ወይንም የኮንስቲትዩሽናል ሞናርኪ ፓርቲም ሆነ የሦሻሊስት ወይንም ኮምኒስት ፓርቲ ሁሌም ቁልፉና ወሣኙ ይህንን ሁሉ ፈትሾ የሚጠቅመኝና የሚበጀኝ ሀገሬንም ሕይወቴንም ወደተሻለ ምዕራፍ የሚያሸጋግረውና የሚለውጠው ይኼ ነው ብሎ በተጨባጭ ምክንያታዊነት የሚወስነው የሚመርጠው ሕዝብ ነው፡፡

የጀርመኑ መራሂ መንግሥት አንጌላ መርክል ፓርቲ ለሦስተኛ ጊዜ ሲመረጥ እሳቸውም ለሦስተኛ ጊዜ በጠቅላይ ማኒስትርነት ሲመሩ ይህን ያደረገው የጀርመን

ሕዝብ በነዚህ ዓመታት ታላቅ የኢኮኖሚ እድገት ለውጥ ስላየ ስላገኘ ነው፤ ሦስት ጊዜ እንዴት ጠቅላይ ሚኒስትር ሆና ትመራለች አላሉም፤ ትልቁ ውጤት ለሀገሪቷና ለሕዝቡ የመጣው ለውጥ ነው፡፡

እነዚህ ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ማክተምና የአንድ ሀገር ሕዝብ የነበሩትንና በግንብ የተለያዩትን ምሥራቅና ምዕራብ ጀርመን አንድ አድርጎ ኃያል ኢኮኖሚና መንግሥት መፍጠር እንደገናም ጀርመን ቀድሞ የነበራትን ጠንካራ ስምና ክብር ተደማጭነት አረጋግጦ ማስቀጠል እጅግ ከባዱና ውስብስቡ ሥራ ቢሆንም ተሳክቶላቸዋል፡፡ የቻይናው ኮምኒስት ፓርቲ በብዙ ውጣ ውረድ ፈተና ውስጥ አልፎ ራሱንም ከውጪው ዓለም አግልሎ ራሱን እየፈተሸ ፖርቲውንም እየገመገመ አመራሩንም እየለወጠና እየተካ ግለኝነትና አምባገነንነትን ሙስናን እያወገዘ እየተዋጋ በብርታት በድል ተመመ፡፡

የውጭ ኃይሎችን ሳይሆን የራሱን ሕዝብና ያለውን የሀገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት ብቻ ተማምኖ በራስ ክህሎትና የሥራ ፈጠራ ፍፁም ሀገራዊና ሕዝባዊ ፍቅር በመንቀሳቀሱ ከ50 ዓመታት በፊት የዓለማችን ድሀ የነበረችውን ሀገር ቻይናን ለዛሬው የዓለም ኢኮኖሚ መሪነት ብሎም ለመላው ዓለም የምትተርፍ ኃያልና ገናና ሀገር እንድትሆን አበቃት፡፡

የፓርቲው አመራር ውጤት ነው፤ ከዚህ ውጪ ቻይናን ማሰብ አይቻልም፡፡ የዓለም ኒዮ ሊበራል ኃይሎችን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቀመር አስደንጋጭ በሆነ መልኩ ሽሮ በዓለም ላይ አዲስ ታሪክ ማስመዝገብ ችሏል፡፡ በዚህም የተነሳ የዓለም የኒዮ ሊበራል ፖለቲካል ኢኮኖሚ የኃይል አሰላለፍ ሚዛን ሳይወድ በግድ ተዛብቷል፡፡ ቀድሞ ወደ ነበረበትም አይመለስም፡፡ ወደ እኛም እውነት ስንመለስ ኢሕአዴግ በአመራር ዘመኑ የቆየባቸው ዓመታት በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ትርጉም ያለው ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ማህበራዊ ለውጥና የፖለቲካ ባህል ለውጦች የተመዘገበባቸው ናቸው፡፡ ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፖርቲዎች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የኒዮ ሊበራል ፖለቲካል ኢኮኖሚ አቀንቃኞችና ደቀመዝሙሮች አፍቃሪ ምዕራባውያንም ስለሆኑ የኢትዮጵያን ፖለቲካና ኢኮኖሚ በእነዚሁ ኃይሎች ፍላጎትና ዓላማ ሥር ለማሰለፍ

የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡ ለህዝባቸውና ለሀገራቸው ሠላምና እድገት ከማሰብ በላይ የውጭ ኃይሎችን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ፍላጎት ለማስፈፀም የሚተጉ ናቸው፡፡

በስም ተቃዋሚ ፖርቲ መስርተው እንገፍ...እንገፍ ቢሉም የፖርቲን ምንነት አያውቁትም፤ በኒዮ ሊበራሉ አካልና አምሳል የተፈጠሩት ስመ ብዙ ብሄራዊና ክልላዊ ፖርቲዎች በንዑስ ከበርቴው በፊውዳሉ (ባላባታዊው) በትምክህተኛው፣ በከበርቴውና ባለቤትነት አቀባባይ ከበርቴው የሚመሩና የጠራ ርዕዮተ ዓለምና ግብ ስለሌላቸው የታችኛውን ሰፊውን ድሀ ኅብረተሰብ ሰለማያውቁት እሱም ሊያውቃቸው አይፈልግም፤ያላቸው ተቃርኖም የማይታረቅ በመሆኑ ለራሳቸው እንጂ ለድሀው ጥቅም አይቆሙም፤ለራሳቸው ሀብት መድለብ መክበር ለበለጠ የሀብት ባለቤትነት ይታገላሉ፡፡

የግሉ ባለሀብትም የውጭ ኢንቨስተሩም ሀብታቸውን በማፍሰስ ለህዝቡም የሥራ እድል በመፍጠር ይስሩ፤ ሀገሪቷ የጀመረችው ልማትና እድገት ለዘለቄታው ይቀጥል ሆኖም ግን መሬት፣ አየር መንገድ፣ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የመሳሰሉት የህዝብና የመንግሥት ሀብት ስለሆኑ አይሸጡም፤ አይለወጡም የሚል ጠንካራ አቋም የያዘው ኢህአዴግ ብቻ ነው፤ በዚህ ምክንያት ነው የኒዮ ሊበራሉ ኃይል ያኮረፈው፤የሀገሪቷን ሀብት ሙሉ በሙሉ በኢንቨስትመንት ስም ወደ ግል ይዞታ መዞር መሸጥ መለወጥ አለበት ባይ ነው፤ ይህ ደግሞ መቼም አይሆንም፡፡

ተቃዋሚው ሰፊውን የሕዝብ ድጋፍ ሊያገኝ የማይችልበትም አንዱ ቁልፍ ነጥብ ይኼው ነው፤ ተቃዋሚ ፖርቲዎች በተደጋጋሚ ለውድቀትና ለክሽፈት የበቁበትም ምስጢር የጠራ ህዝባዊ አጀንዳና መስመር ማጣት፤ በውጭ ኃይሎች በተቀረፀ አጀንዳ መመራት፤ በጥላቻና በእብሪት በግብዝ አስተሳሰብ መዘፈቅ፤ ከእኛ በላይ ኢትዮጵያዊ የለም የሚል ሌላውን ዜጋ የመናቅ ልዩነትን ያለመቀበል በሀሰት ወሬና ፕሮፓጋንዳ በስም ማጥፋትና በፈጠራ ወሬ ተነክሮ መዳከር ለሀገርም ለህዝብ በማይጠቅም እኩይ ተግባር ተጠምዶ ሲላቸውም ከሀገር ጠላት ጋር ተሰልፎ ሀገርን መውጋት የውድቀታቸው ምክንያቶች ነው፤ የህዝብ አመኔታና ክብር ያጡትም በዚሁ ነው፡፡

ኢሕአዴግ ሕዝብን ያቀፈና ያሳተፈ የሕዝብን ትርታ የሚያዳምጥ ለታችኛው ኅብረተሰብ የቆመ ፖርቲ ወይንም ግንባር በመሆኑ በጠንካራ የሥራ ባህል በመሥራት ታላላቅ ሀገራዊና አህጉራዊ የድል ውጤቶችን አስመዘግቧል፤ በዲፕሎማሲውም መድረክ ተሰሚና ተደማጭና ተጽዕኖ ፈጣሪ ለመሆን ችሏል፤ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፖርቲዎች የፖርቲ ፖለቲካ ሥራን የፖርቲን ምንነትና አሰራር ሀ ብለው ከኢህአዴግ መማር አለባቸው፡፡

እንቅብ ሙሉ ተቃዋሚ ፖርቲ ቢሰበሰብ ያረጀ አስተሳሰብ ኋላ ቀርና እጅግ የወረደ፣ የዘቀጠ፣ የጐጥ፣ የጥላቻ፣ የጀብደኝነትና የአምባገነንነት አመለካከትን ተሸክሞ የትም መድረስ አይታሰብም፤ ለዚህች ትልቅ ሀገር ለኢትዮጵያ ሊበጁ ቀርቶ ለራሳቸውም መሆን አይችሉም፡፡ ሀገር ውስጥ ያሉትም አሜሪካና አውሮፓ ሆነው ከሻዕቢያ፣ ከግብፅ፣ ከአልሸባብ ጋር ተሰልፈው የሚያፍጫጩትም ጽንፈኛ ተቃዋሚዎች ጭርሱንም ለኢትዮጵያ አይመጥኑም፡፡ በድሮ በሬ ያውም ባረጀ በሬ ለማረስ የሚከጅሉ ናቸው፡፡በሰለጠነና ባደገ ሀገርና ህዝብ ውስጥ ቢኖሩም የሰለጠነ የፖለቲካ አስተሳሰብ የላቸውም፤አብሮነትን፣ ተቻችሎና ተከባብሮ ልዩነትን ውበትና ጥንካሬ አድርጎ ለጋራ ሀገር በጋራ መሥራትን አይቀበሉም፡፡

ጤነኛ አመለካከትና አስተሳሰብ ያላቸው ቢሆን ኑሮ ሰፊ ማስተዋል እርጋታ ማመዛዘን ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ በመሠረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ እውቀታቸውን እያካፈሉ በሚቃወሙት ይቃወሙ ነበር፡፡ ምክንያቱም አንድ ፖርቲ ሥልጣን ያዘ፣ መራ፣ ለቀቀ፣ ሌላ ፖርቲ መጣ ኢትዮጵያም ኢትዮጵያ ሀገራቸው ሕዝቡም የራሳቸው ወገን የሆነ ሕዝብ ነው፡፡

ኢሕአዴግ ማንም ሊከደው በማይችለው መልኩ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለውጧል ሲባል መሬት ላይ የሚታይና የሚጨበጥ ከትውልድ ትውልድ የሚያኮራ ሥራ ነው የሰራው፡፡መሪዎቹ እንደ ሰው ሊደክሙ ሊያረጁ ሊታመሙ ሊሞቱ ይችላሉ፡፡ ፖርቲው ግን አይሞትም፡፡ የዓለምን ፖለቲካ ተጨባጭ እውነት እያነበበ በአዲስ አስተሳሰብና በአዲስ ኃይል እየተገነባ ለወቅቱም የሚመጥን አመራር እየሰጠ ይቀጥላል፡፡ ጠንካራ ተቋም ጠንካራ ፖርቲ እንዲህ ነው፡፡

እነማኦ ዜዱንግ በተፈጥሮ ሕግ አርጅተው ስለሞቱ የመሠረቱት ፖርቲ አልሞተም፡፡ ሕዝባዊና ሀገራዊ በመሆኑ ባለቤቱም ሕዝብ ስለሆነ ሀገራቸውን ከድህነት ለማውጣት አዳዲስ ስትራቴጂና ፖሊሲ በማውጣት ዓለምን ተዓምር ያሰኘ የዓለም የኢኮኖሚ ቁንጮ የበላይ ለመሆን ያስቻለ ደረጃ ላይ ደረሱ፡፡

ከረሀብ፣ ከችግር፣ ከድህነት የወጣው በእውቀትና በቴክኖሎጂ የገሰገሰው ከራሳቸው አልፈው ለመላው ዓለም የተረፉት ከተረጅነት ቀንበር የተላቀቁት መላው ቻይናውያን ናቸው፡፡ እንደ እኛ ትልቅ ሀገር ያልተነካና ያልተበላ የተፈጥሮ ሀብትና ድንግል መሬት ንፁህ አየር የውኃ የቡና የጥራጥሬ የቀንድ ከብት ወዘተ ሀብትና ስጦታ ይዞ ለፍተውና ደክመው ሀገር እየለወጡ ያሉትን በማጥላላት ጥቀርሻ በመቀባት ተመልሰን ወደምፅዋትና እርዳታ ለማኝነት እንድንገባ እርስ በእርስ እየተባላን እንድንቀጥል፤ሥራና ምርት እድገትና ለውጥ መሻሻል እንዳይኖር እንዳይመጣ ለማድረግ የጠላት መሣሪያ ሆነው የተሰለፉትን የጽንፈኛው ዲያስፖራ ጀሌዎችና ፖርቲዎቻቸውን ሕዝብ ማየትም መስማትም አይፈልግም፡፡ የትኛውም ዓይነት ዘረኝነትም ሆነ ኃይማኖታዊ አክራሪነት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧም አይበጅም፤ ልናየውም አንፈቅድም፡፡

ድሮም ሀገሪቷን የገደሏት ለውጪ ጠላት ተላላኪና አሽከር በመሆን በራሳቸው ሀገር ላይ እየተሰማሩ በባዕዳን ኃይሎች ጉዳይ አስፈፃሚነት ተሰማርተው እርስ በእርስ እየተናከሱና እየተባሉ ሲጠፉፉ መኖራቸው ነው፡፡ ዛሬ ሀገሪቷ ይኼ ችግር ተደግሞ ማየት አትፈቅድም፤ ሕዝብና መንግሥት ተባብረው እስከሰሩ ድረስ ከቀድሞውም የበለጠ ለውጥና እድገት ይመጣል፡፡

አሁን ሀገሪቷ የደረሰችበት የለውጥና የእድገት ደረጃ ሲታይ በእርግጠኝነት 100 ዓመታትን ወደፊት እንደተራመድን አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡ በብዙ መስክ ታላላቅ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡ ይኼንን የበለጠ አጠናክሮና ጠብቆ ለዘላቂ እድገት መትጋት፤ አጠናክሮና ጠብቆ ለላቀ እድገት መሥራት ብቻ ነው የሚጠበቀው፡፡

ይህንን እድገትና ልማት በወሬ፣ በአሉባልታ፣ በሐሰት ፕሮፖጋንዳ፣ በውዥንብር፣ በሁከትና በአመፅ እናጨናግፋለን ብሎ የሚያስብና የሚያሰላ ተቃዋሚ በምንም

ዓይነት መስፈርት ሀገሬ ወገኔ ሊል አይገባውም፡፡ ይልቁንም ፀረ ኢትዮጵያና ሕዝቧ ሆኖ የቆመ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው፡፡ ተቃዋሚው ፖለቲከኛ ስለፖለቲካ፣ ስለ ሀገር፣ ስለ ሕዝብ ምንነት አንድም ምንም የጠለቀ እውቀትና ግንዛቤ የሌለው በጥላቻ ፈረስ የሚጋልብ ሀገራዊ ራዕይ አልባ  መሆኑን አስረግጦ ያሳያል፡፡ የረባ ተቃዋሚ የለም የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡

ነገ እድሉን ካገኘ የሚመራት ሀገርና ሕዝብ ነው፤ እድገቷን እንጂ ውድቀቷን ማየት አልሻም የሚል ተቃዋሚ አይደለም ያለው፡፡ በአሜሪካን የዴሞክራቱና የሪፐብሊካኑ ፓርቲዎች በምርጫ ወቅት ካላቸው ጠንካራ ፉክክር በተጨማሪ በሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂም ሰፊ ልዮነቶች አሏቸው ፤ይህም ሆኖ በሀሳብ የበላይነት ይፎካከራሉ፤ ይከራከራሉ፤ ሕዝብ በድምፁ የሚደግፈውን ያሳልፋል፣ ሁለቱም የአሜሪካንን ብሄራዊ ጥቅም በተመለከተ  ልዮነት የላቸውም፡፡

በጥላቻና በጐሣ ጉዳይም አይናቆሩም፡፡ በሕጉ መሠረት የመጨረሻው በሕዝብ ድምፅ በበላይነት ካሸነፈው ፓርቲ ጋር በመሆን ለሀገራቸው በጋራ እየተመካከሩ መሥራቱን ይቀጥላሉ፡፡ የእኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በፖለቲካ አስተሳሰብና እውቀት ገና ያልበሰሉ ጥሬዎች ናቸው፡፡ ለእነሱ ተቃዋሚነት ማለት ገዥው ፖርቲ የሚሰራውን ሁሉ በሙሉ መቃወም ነው፤ ለእኛ ተቃዋሚዎች ተቃዋሚነት ማለት መንግሥትን መሪዎቹን መሳደብ፣ መዝለፍ፣ ስም ማጥፋት ማለት ነው፤ በግብዝነት ከእኛ በላይ ለሀገር ለሕዝብ አሳቢ ተቆርቋሪ የለም፤ እኛ ያልነው ሀሳብ ብቻ ነው ትክክል፤ ሌላው ተቀባይነት የለውም ባይ ናቸው፡፡ የሀሳብ ልዩነትን ማየትም መስማትም አይፈቅዱም፡፡

ከእነሱ የተለየ ሀሳብ ያፈለቀ ያመነጨ ሁሉ በስርጐ ገብነት በአድርባይነት ይፈረጃሉ፤በሀሳብ የበላይነትና በምክንያታዊ ክርክር አያምኑም፤ በጉልበት፣ በዱላ፣ በድብድብ፣ በጡንቻ የተለየ አመለካከት ያለውን ለማስገበርና ለማንበርከክ ብዙ ርቀት ይሄዳሉ፤ከስም ማጥፋት ጀምሮ ግለሰቦችን ለማግለል የሥነ ልበና ጦርነት ይከፍታሉ፡፡

ከእነሱ የተለየ አስተሳሰብ ካለው ሰው ጋር ለምን አብራችሁ በላችሁና ጠጣችሁ፤ ለምን ጓደኛና ቤተሰብ ትሆናላችሁ ለምንስ ከእነሱ ጋር ትታያላችሁ፣ ከሱቃቸው፣

ከገበያቸው ትገዛላችሁ፤ ሰርግና ለቅሶ ለምን ትደራረሳላችሁ የሚል እጅግ የዘቀጠ እጅግ የወረደ የአስተሳሰብ አድማሱ የጠበበና የተራቆተ ሥነ ምግባር የሌለውና ቦዘኔያዊ ባሕርይና ድርጊት የተጣባው ተቃዋሚ ነው ያለው፡፡ እነዚህ ሀገር እንመራለን ብለው ሲያስቡ ያሳፍራል፤ያስፈራልም፡፡

ሀገርም ፖለቲካም በላቀ የአስተሳሰብ ምጥቀትና በሰፊ አስተዋይነት ነው ሊመራ የሚችለው፤ እነዚህ ሰዎች (ተቃዋሚው) ሥልጣን ቢይዙስ ቢያገኙስ ምን ያደርጋሉ ተብሎ ሲታሰብ እጅግ የከፋ አምባገነኖችና ፋሽስቶች በመሆን ያልተጠበቀ ጥፋትና መዓት ሊያመጡ እንደሚችሉ በርካታ ዓመታት በተደጋጋሚ ከታየው የማይደበቅ ባህርያቸው በመነሳት መናገር ይቻላል፡፡ ሕዝቡም አይቶና መዝኖ ነው የተቃዋሚውን ወሬና ፕሮፖጋንዳ አልሰማም በቅታችሁኛል ያለው፤ ተቃዋማው ዛሬ በምርጫው ዋዜማ ግርግር ለመፍጠር የሚከጅለው ደካማና አቅመ ቢስ መሆኑን ስለሚያውቅ ነው፡፡

የራሱን መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት ያልቻለ ወደ ውስጡ መመልከት የተሳነው በራሱ ውስጥም በውጭም ለውጥ ለማምጣት የማይችል መሆኑን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ግርግር ሁከት ተቃውሞ ሰልፍ ጫጫታ ለመፍጠር ይከጅላል፡፡ በለሊትና በቀን ለነሱ ሰልፍ ሥራ የሚፈታና አዳማቂ የሚሆን ሕዝብ የለም፡፡ ከምርጫው ጋር በተያያዘ የውጭው ፅንፈኛ ዲያስፖራ አውጥቶት ወደ ሀገር ቤቱ ተቃዋሚ የላከው የቀለም አብዮቱ እቅድ በአደባባይ ሕግና ሥርዓትን መጣስና ሙሉ በሙሉ ሕግና አለማክበር የሚለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ የትም አያደርስም፡፡ አንዲት እርምጃም አያራምድም፡፡

ሕግና ሥርዓት ሲጣስ መንግሥት ሕግና ሥርዓት የማስከበር ግዴታም ኃላፊነትም አለበት፡፡ ሥርዓተ አልበኝነትን መፍጠር ሁሉም ነገር ከቁጥጥር ውጪ እንዲሆን ሥራና ትምህርትም ትራንስፖርትም ወዘተ እንዲቆም እናደርጋለን ብለው ቢያቅዱም አልተሳካም፡፡ ብዙ ጊዜም አቅደው ከሽፋል፤ አሁንም ይከሽፋል፡፡

የዓረቡን አለም አብዮት ወደ ኢትዮጵያ እናመጣለን የሚለው የፅንፈኛው ዲያስፖራና የኢንጂነር ይልቃል እንገፍ...እንገፍ በኢትዮጵያ ምድር ላይ መቼም አይደረግም፡፡የከሸፈውም የሚከሽፈውም በሕዝቡ ነው፡፡ ምክንያቱም በዓለም ሕዝብ

ፊት የታየው የሀገራትና የሕዝቦቿ ወድመትና ሞት በኢትዮጵያ ተደግሞ እንዲታይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለማይፈቅድ ነው፡፡

በምርጫ 2007 ያለአንዳች ጥርጥር በተሰሩትና በተገኙት ሀገራዊ ለውጦችና እድገቶች በጅምር ላይ ባሉትና መጠናቀቅም በሚገባቸው ሥራዎች ሀገሪቷንም ጠብቆና አስከብሮ እየመራት ስለሚገኝ ተቃዋሚው በራሱ ችግር የተጠለፈና እየተፍገመገመ ያለ በመሆኑ ተቃዋሚው እንደ ተለመደው ምርጫው ተሰረቀ ተጭበረበረ ቢልም እድገትና ልማቷን በብቾኝነት የሚያስቀጥለው ኢሕአዴግ በአብላጫ የሕዝብ ድምፅ ይመረጣል፡፡

የትኛውም ተቃዋሚ ፓርቲ አንድነትና መኢአድም መድረክም ሌሎችም የክልሎች በምርጫው በመሳተፍ የተወሰኑ ድምጾችን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ይኼም ያጠራጥራል፤ ነገር ግን በአጠቃላይ የበላይነት ድምፅ በማግኘት የሚመረጠው ገዥው ፓርቲ ነው፡ ፡ የሚያስመርጠው እጅግ ብዙ ጠንካራና ብርቱ ጐኖቹ ሀገር ለመለወጥ የሰራቸው ተጨባጭ ሥራዎቹ ናቸው፡፡

ተቃዋሚውን የሀገር ኃላፊነት ለመረከብ የሚያበቃው ተመራጭ የሚያደርገው ምንድነው የሚለውን ሕዝቡ ራሱ ጠይቆ ራሱ መልሶታል፡፡ እርስ በእርስ የሚባሉ ሰዎች ነገ ደግሞ ሥልጣኑ ለእኔ ይገባል የለም ለእኔ ነው በሚል አሳፋሪ ባህርያቸው ሀገርንና ሕዝብን አደጋ ላይ እንዲጥሉ የሚፈቅድ ህዝብ የለም፡፡